Wednesday 11, 2011

# ንስሀ እና ጥቅሙ

ንስሀ ማለት ወደ እግዚአብሔር በሙሉ በመመለስ እንደገና ወደ ኋላ ላለመመለስ መወሰንና ማሰጠት ነው፡ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚስማማ የእንግሊዝኛ ትርጉም፡ -

“Repentance is the act of turning from sin and making a commitment not to return. Doing a complete turn around changing directions making a decision to put away the old man.”(David Wilkerson)

ንስሀን በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡የመጀመሪያው የንስሀ አይነት ስር ነቀል ዋጋ ከፍለን ወደ ጌታ ለመመለስ የምንከፍለው እርምጃ ነው፡፡ይህ መንፈሳዊ እርምጃም ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሀን ያሸጋግረናል፡፡ከነበርንበት ማጥ አውጥቶ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት እንድንገባ ያደርገናል፡፡ይህ የንስሀ አይነት በህይወታችን ትልቅ እና ወሳኝ እርምጃ ከመሆኑም የተነሳ ወደ ህይወታችን የሚመጣው የሰላም፣የደስታ እና የእረፍት ለውጥ ቀላል አይደለም፡፡

ሁለተኛው አይነት ንስሀ ወደ ጌታ ከላይ በተጠቀሰው እርምጃ ወደ ቤቱ ከመጣን በኋላ ወደ እርሱ እስከምንሄድበት ቀን ድረስ እለት እለት የምናከወነው የክርስትናችን የጀርባ አጥንት ነው፡፡አንድ የእግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ያሉትን ሰው በእጅጉ እንደሚባርክ የተናገሩት ነገር ወስጤ ታትሞ ቀርቷል፡፡እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡ -

- ንስሀ የሚገባ ልብ(repentant heart)

- ፈውስን የሚጠብበቅ ልብ(expectant heart)

እውነተኛ ንስሀን የሚለማመድ ሰው በህይወቱ ለሚገርም በረከት የእግዚአብሔርን ልብ ያዘነብላል፡፡እውነተኛ ንስሀም ህይወትን አድሶ ለማቆም ዋነኛ መንገድ ነው፤የእግዚአብሔርን የሚጽናናትና የሚደገፍ ክንዱን የምንቀምስበት!መኪና እንደልብ እንዲንሸራሸር የተደፈኑት የዘይት ቧንቧዎቹ ማጠረግ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ ከተጠለለፍንባቸው እግዚአብሔርን ከሚያሳዝኑ ሀጢያቶች እና ርኩሰቶች የምንጠራበት መንገድ ንስሀ ነው 1ዮሀ 1፡9 እንዲህ እንደሚል ፡-“በሀጢያታችን ብንናዘዝ ሀጢያታችንን ይቅር ሊለን ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን የታመነ ጻድቅ ነው”፡፡እጅግ የሚደንቅ ቃል ነው፡፡”ከአመጻም ሁሉ ሊያነጻን” የሚለው ቃል ላይ እንድታሰምሩልኝ እፈልጋለሁ፡፡እጅግ የሚደንቅ የተስፋ ቃል ነው፡፡ከአንዳንድ ሀጢያት ሳይሆን እግዚአብሔርን ካሳዘንባቸው ማንኛውም ነገሮች ሁሉ እንደሚል ልናስተውል ይገባል፡፡“ሊያነጻን” የሚለው ቃል ሊያጥበን፣ሊፈውሰን ፣ሊያጠራን ወዘተ የሚል ትርጉም ይዟል፡፡ይህ የመንፈስ ቅዱስን ወስጥን የሚጽዳትን ሀይል እና የማጽሚ ስራን በሚገባ ያሳየናል፡፡አዎ ከልብ በእውነትና በመንፈስ የተጸለየ የንስሀ ጸሎት ወስጥን በሚገባ ያነጻል፣ያድሳል፣እንደገናም ያቆማል፡፡

ኢሳ 1፡18 ላይ “ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ሃጢያታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች”የሚል ገራሚ ቃል እናገኛለን፡፡ይህ ቃል የንስሀን ወስጥን በፍጹም የሚለውጥ ሀይል ምሳሌያዊ በሆነ ሚልኩ የሚገልጽ ሲሆን ሁለት በምንም ሚልኩ የማይገናኙ ነገሮችን እያወዳደረ እናያለን፡፡እንደዚህ አስቀምጫቸዋለሁ፡ -

- አለላ (ደማቅ ቀይ በስሱ ከቢጫ ቀለም ጋር የተደባለቀ ቀለም–scarlet) ---------->አመዳይ(እንደ በረዶ ነጭ)

- ደም (ደማቅ ቀይ-crimson) -------------> ባዘቶ(እንደ ሀር ነጭ)

ከላይ ያሉት ንጸጽሮች በምንም ሚልኩ እጅግ የተራራቁ እንደሆኑ ሁሉ ከልብ የተደረገ ንስሀም ወስጣችን በእንዴት አይነት ሁኔታ ሊቀይር እንደሚቻል ነው የሚያስገነዝበን፡፡አዎ ንስሀ ወስጣችንን የማስሚርና ከጌታ ጋር ያለንን ህብረት በሚባ የሚደስ ሀይል አለው፡፡

ንስሀ ማለት ምን ማለት ነው ተብዬ ብጠየቅ መዝ 51 ነው ብዬ የምሜልስ ይመስለኛል፡፡መዝ 51 በመግቢያ ላይ እንደተገለጸው "ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ የዳዊት መዝሙር"ብሎ ነው የሚጀምረው፡፡ዳዊት ያንን የዝሙት ሀጢያት ካከናወነና እና የግድያ ወንጀልን በኦርዮ ላይ ከፈጸመ በኋላ ሀጢያቱን ሳይናዘዝ ወደ አንድ አመት ገደማ እንደቆየ የመጽሀፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ያንን ሀጢያት በእራሱ ደፍሮ መናዘዝ ስላቃተው ነው እግዚአብሔር ነቢዩ ናታንን የላከው፡፡ዳዊት በሀጢያት ወስጥ ሆኖ ያለወን ህይወት አስቀያሚ ጎጂነት በመዝ 38፡4-10 ላይ እንዲህ ብሎ ይናገራል፡-

"አቤቱ፥ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፥ በመዓትህም አትገሥጸኝ።
ፍላጾችህ ወግተወኛልና፥ እጅህንም አከብደህብኛልና።
ከቍጣህ የተነሣ ለሥጋዬ ጤና የለውም፤ ከኃጢአቴም የተነሣ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም።
ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ እንደ ከባድ ሸክምም በላዬ ከብዶአልና።
ከስንፍናዬ የተነሣ ቍስሌ ሸተተ በሰበሰም፤
እጅግ ጕስቍልሁ ተዋረደህም፥ ሁልጊዜም በትካዜ እመላለሳለሁ።
ነፍሴ ስድብን ተሞልታለችና፥ ለሥጋዬም ጤና የላትምና።
ታመምሁ፤ እጅግም ተቸገርሁ፥ ከልቤ ወዘዋዜም የተነሣ ጮኽሁ።
አቤቱ፥ ፈቃዴ ሁሉ በፊትህ ነው፥ ጩኸቴም ከአንተ አይሰወርም።
ልቤ ደነገጠብኝ፥ ኃይሌም ተወችኝ፥ የዓይኖቼም ብርሃን ፈዘዘ።"

አዎ ሀጢያት ጉስቁልና አለው፣እፍረትና የወደደት ስሜት አለው፣ጭንቀት አለው፣ትካዜ አለው፣ድካም አለው፣ህመም አለው፣ድንጋጤም አለው(እነዚህን ችግሮች ጥቅሶቹ ወስጥ አንድ ባንድ ማየት ይቻላል)፡፡ከላይ እንደጠቀስሁት ዳዊት ለብዙ ወራት በእንደዚህ ያለ ስሜት ወስጥ ሰንብቷል፡፡እግዚአብሔር የምህረት አምላክ ስለሆነ ነቢዩ ናታንን ላከበትና ጉዱን ገለጠበት፡፡ከዚያም ዳዊት በእንዴት አይነት የልብ ማስበር ወስጥ እንዳሳለፈ ነው መዝ 51 የሚገረን፡፡የጸለየወም ጸሎት ወደር የለወም እጅግ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያዘነብል ነበር፡፡ይህን ክፍል ከመቶ በላይ አንብቤዋለው፡፡በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ስሆን መጀመሪያ የማበወም ክፍል ነወና በሀይል እወደዋለሁ፡፡
በዚህ መዝሙር ንስሀ ወስጥን ለማንጻት እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ የሚያሳየን ቁጥር 7 ነው፡፡እንዲህ ይላል፡-"በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ እጠበኝ ከበረዶ ይልቅ ነጭ እሆናለሁ፡፡"ይህ ቃል ከኢሳ 1፡18 ተመሳሳይነት አለው፡፡አዎ በቅንነት እና እግዚአብሔርን በመፍራት የተጸለየ እወነተኛ ጸሎት ከብዙ የከፋት ትርፍ ይገላግላል፤ወስጥን ይቀይራል ያሳምራልም፡፡

ከልብ የተጸለየ የንስሀ ጸሎት ወስጥን በሚደስ የማርም ማኮታዊ ደስታ ወስጥ ይከታል፡፡በእራሴ ህይወት የእግዚአብሔርን መንፈስ በሆነ ሀጢያት ማስዘኔ ሲገባኝ ሁለንተናው ገደል ነው የሚሆነብኝ፡፡ባዶነት ይሰማኛል ጭው ይልብኛል እደነግጣለሁም፡፡ከዚህ ስሜት የሚላግለኝ እግሩ ስር በእወነትና በመንፈስ መደፋት ነው፡፡ሌላ አማራጭ እንደሌለ ገብቶኛል፡፡ዳዊት መፍትሄወን መዝ 51:7 ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡-"ሀሴትንና ደስታን አሰማኝ የሰበርሀቸወንም አጥንቶቼም ደስ ይላቸዋል፡፡" "የሰበርሀቸው አጥንቶቼም" የሚለው ሀረግ በሀጢያት የምንከፍለወን የዋጋ ከባድነት ያሳየናል-ጥልቅ መሆኑንም ጭምር!

መዝ 51፡17 ላይ "የእግዚአብሔር መስዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው"እንደሚል ዳዊት በተሰበረ መንፈስ የእግዚአብሔር ፊት ፈለገ፣አነባ፣ቃተተ፣ጾመ፣በእግዚአብሔር ፊት እራሱን ጣለ፡፡ስለዚህም ዳዊት ደጋግሞ በቀደመው ዘመን በጌታ ፊት ያገኝ የነበረወን የመታደስ በረከት በጸሎት ቋንቋ ሲገልጸው ነው የምንገነዘበው፡፡አንዴ ብቻ ሳይሆን የጌታን የማዳን፣የሚጽናናት፣የሚደስና ደግፎ የማቆም ጉልበት በህይወቱ መቅመሱን በዚህ መዝሙር ወስጥ ያሉ አገላለጾች በሚባ ያሳዩናል፡፡

በዚህ ጽሁፌ እኔም ላሳይ የፈለግሁት ዋና ቁም ነገር ለትምህርታችን የተጻፉትን የንስሀ መርሆዎች በማስተዋልና ተግባራዊ በሚድረግ ግልብ ከሆነ የንስሀ ህይወት ወደ ጠለቀ ህብረትና ግንኙነት የሚከት የንስሀ ህይወት እንዲኖረን ለማሰብ ነው፡፡ስለዚህ በተለያዩ ከጌታ መንገድ ወጣ ያሉና መንፈሱን የሚያሳዝኑ ነገሮችን ስናደርግ ማንኛወንም ነገር አቁመን በሚባ ለመመለስ መንፈሱ እንደሚሠራን በመሆን እርምጃዎችን እንወሰድ፡፡በንስሀ ዙሪያ የተጻፉ የእግዚአብሔር ቃሎችን በማስላሰልና በማጥናት በጸጋው ዙፋን ፊት ሆነን ልባችንን እናፍስስ፡፡ካስፈለገም እንደ ጴጥሮስ ምርር ብለን እናልቅስ እናንባ፡፡ሚር

5፡ 29 ላይ "ከስቃይዋ እንደዳነች በሰውነቷ አወቀች" እንደሚል በውስጡ ማፈሳችን የጌታ ፈውስ እስኪታወቀን ፊቱን እንፈልግ ከወደቅንበትም እንነሳ፡፡ሀጢያቶቻችንንም ስም ሰጥተን እያንዳንዱን ጉድ በእውነትና በቅንነት እንናዘዝ፤እናም ሙሉ በሙሉ ለመጣስ እንወስን፡፡ያኔ በሚያስደንቅ ምህረቱ ከተፍ ብሎ ይፈውሰናል፤ይጠግነናል ያስደንቀናልም፡፡የ "እንደገና" አምላክ ነውና እንደገና ሌላን እድል ይሰጠናል፡፡ፍቅሩ እጅግ ታላቅ ነውና እንደገና ጸጋን ጸጥቶ ያቆመናና ካሰብነውና ከለመነው በላይ የፍሬ ሰዎች ያደርገናልና ፊቱን እንፈልግ!አሜን!

ጌታ ይባርካችሁ!

በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

240-330-5004

beke_abay@yahoo.com